ስለአዲሱ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013፡- አንዳንድ ምልከታዎች

1. የአዋጁ መልካም ጎኖች፡-

1.1. የተለያዩ አዋጆችን አንድ ላይ አጠቃልሎ/consolidated/ ለአጠቃቀም ምቹ ማድረጉ፣

1.2. በፍርድ ሊወሰኑ በሚችሉ ጉዳዮችና በሕገ መንግስታዊ መብቶች ላይ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ያላቸው መሆኑን ግልጽ ለማድረግ ጥረት ማድረጉ፣

1.3. ስለመሰረታዊ የሕግ ስህተት አመላካች ሊባሉ የሚችሉ መስፈርቶችን ማስቀመጡ፣

1.4. የክልል ጉዳዮች ወደ ሰበር ችሎቱ ሊመጡ የሚችሉበትን አግባብ/መንገድ/ ለማጥበብ መሞከሩ፣

1.5. የሰበር ችሎት ውሳኔ አስገዳጅነት የሚጀምርበትን ጊዜ ማሳየቱ (ባይታተምም)፣

1.6. የሰበር ችሎት ውሳኔ የሚቀየርበትን ስርዓት የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው ማድረጉ፣

1.7. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን መጨመሩ፣

1.8. የአለም አቀፍ ድርጅቶች በፍትሃ ብሔር ሊከሰሱ የሚችሉበት አግባብ ካለ ክስ ሊቀርብባቸው እንደሚችል የሚያሳይ ድንጋጌ መያዙ፣

1.9. ፍርድ ቤቶቹ በበጀትና በድጋፍ ሰራተኞች አስተዳደር ረገድ ነጻነት እንዲኖራቸው ማስቻሉ፣

1.10. ከዳኝነት አገልግሎት አስጣጥ ጋር በተያያዘ አጋዥ መመሪያዎች ሊወጡ የሚችሉበትን አግባብ መደንገጉና እንደ አስማሚ መርና የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ያሉትን አዳዲስ ሀሳቦችን ማካተቱ፣

1.11. ከዳኞች ከችሎት የመነሳትና ከውሳኔዎች/ትዕዛዛት አፈጻጸም ጋር ተያይዞ አስተማሪ ቅጣቶች ሊጣሉ የሚችሉበትን አግባብ የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን መያዙ.....ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።

2. የአዋጁ ውስን ድክመቶች

2.1. መግቢያው ላይ ስለአዋጁ ዓላማዎች ሲዘረዝር የፌደራል ጉዳዮችን ለመለየት ብሎ ያለመጥቀሱ፣(አዋጅ ቁጥር 25/88 ግን ይህንኑ በመግቢያው ላይ ይገለጽና አዲሱ አዋጅ የያዛቸውን ሌሎች ነጥቦችን አይጠቅስም ነበር (ቁንፅል መግቢያ ይዞ ነበር)፣

2.2. የአርትኦት ስራ ግድፈት መኖሩ- የአማርኛም ሆነ የእንግሊዝኛ ፊደላት እና ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች መኖራቸው

ለምሳሌ፡-

o የአማርኛ ስርዓተ ነጥብ የሆነው ነጠላ ሰርዝ በብዙ ቦታዎች ከቃላት እንዲርቅ መደረጉ፣ ባንዳንድ ቦታዎች ደግሞ በነጠላ ሰረዙና በቀጣዩ ቃል ወይም ሐረግ መካከል ክፍተት/ስፔስ/ ሳይኖረው መቅረቱ፣ በቃላት ወይም በሐረጎች መካከልም ስፔስ መኖር ሲገባው መታለፉ፣

o ፌደራል የሚለው ቃል በብዙ ቦታዎች(ምሳሌ በአንቀጽ 3(1) ፣ አንቀጽ 4 የመጀመሪያው ፓራግራፍ፣ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16 "ደ" ከተባለ በኋላ በሌሎች በርካታ ድንጋጌዎች ስር በፊደል "ደ" መተካቱ፣ በብዙ አዋጆች የነጋሪት ጋዜጣ ስያሜም ሆነ ተቋማት ስም ሲገለጽ ፌደራል የሚል እንጂ ፌደራል የሚል ሁኖ አይታይም፣

o አንቀጽ 3 (2) ስር ድንጋጌዎች መባል ሲገባው ደንጋጌወች ተብሎ መታለፉ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 5(1(ደ)) ስር ወሳኝ ኩነት የሚለውን ሐረግ ወደ እንግሊዝኛ ሲተርጉም Critical Event (ስለወሳኝ ኩነቶች የሚደነግገውን አዋጅ ቁጥር 760/2004 እንኳን ባለማገናዘብ (Vital Events)) ብሎ ማስቀመጡ፣

o በአንዳንድ ድንጋጌዎች ስር ፍርድ ቤቶች የሚለውን ቃል በፍ/ቤቶች መተካቱ (አዋጅ ላይ አሳጥሮ መግፍ ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ወጥነት ያለመኖር)፣ ለምሳሌ በአዋጁ አንቀጽ 17(1(ተ))፣ በአንቀጽ 37(1)(2)(4)

o በአዋጁ አንቀጽ 5(1(ደ)) እቁብ የሚለውን ቃል association በሚል መተርጎሙ(እቁብ በፈረንጅ አገር የሚታወቅ አይመስለኝም፣ አገር በቀል ማህበራዊ ተቋም ስለሆነ እንዳለ ቃሉን Equb ብሎ በአዋጁ ማስቀመጥ የማይቻልበት አግባብ አለ ብዬ ስላላስብኩ)፣

o በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር ስለሚኖሩ ችሎቶች ሲደነግግ(አንቀጽ 25) የፍትሃ ብሔርና የወንጀል የመጀመሪያ ደረጃ ችሎቶች እንዲሚኖሩት መግለጹ በአዋጁ አንቀጽ 8 ስር ከተደነገገው ጋር የማይጣጣም መሆኑ(ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ያለው ብቸኛው ስልጣን ከስልጣን ይለይልኝ ጋር የተያያዘ ነው)። በዚህ ረገድ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ደግሞ በጣም ውስን(እንዲያውም የማይቀርቡበት የበጀት አመትም ነበር) ስለሆነ ለእነዚህ ጉዳዮች ብሎ የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ያለውን ችሎት ማደራጀት የሰው ሃይልን ብክነት ያስከትላል፣(ምናልባት ይህ አባባል በአዋጁ እንዲሰፍር የተደረገው ከዚህ በፊት የነበረውን አዋጅ በመቅዳት ሂደት በተፈጸመ ስህተት ወይም ስልጣን ይለይልኝ የሚለው ጉዳይ ስላለ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን ብዥታ ለማስወገድ ሊሆን ይችላል)፣

o በአዋጁ አንቀጽ 23 (1(ሐ)) ስር መጨረሻ ላይ ....13241... የሚለው ቁጥር ያለምክንያት ገብቶ መታተሙ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 4(16) ስር በአማርኛው ቅጅ የማስረጃ ሕግ የሚለው ሐረግ በእንግሊዝኛው ቅጅ Procedure Code በሚል የተተረጎመ ሁኖ መታየቱ፣ በዚሁ ድንጋጌ ስር በእንግሊዝኛው ትርጉም ውስጥ የመጀመሪያው ወርፍተ ነገር ከአለቀ በኃላ አዲስ በሚጀምረው ወረፍተ ነገር ውስጥ other የሚለው ቃል በ“ካፒታል” O መጀመር ሲገባው በ”ስሞል“ o መጀመሩ፣ እንዲሁም In addition to የሚለው ቃል አርፍተ ነገሩ ባላለቀበት ሁኔታ I በካፒታል ሌተር መጻፏ፣

o በአንዳንድ አንቀጾች ስር ፊደሉ ”ስ ” መሆን ሲገባው ”ሰ“ ተብሎ መጻፉ(ለምሳሌ በአንቀጽ 19(1(ረ)) ስር ....ሰለተፈጻሚነቱም... በሚለው ቃል ስር ያለው፣ በአንቀጽ 36(2) ስር ....ማሰገባት.... የሚለው ቃል፣በአንቀጽ 47(4) ... እሰከ.... ፣ በአንቀጽ 55(2) ስር ...ለማሰፈጸም... የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

o በአዋጁ አንቀጽ 53 ስር በአማርኛው ቅጅ ...ባለሙያዎች... መባል ሲገባው ....ባለሙያወች... መባሉ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 50 ስር ቴክኖሎጂ መባል ሲገባው ቴክኖሎጅ መባሉ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 26(3) ስር የክልል የሚለው የአማርኛ ቅጅ በእንግሊዝኛው reginal በሚል መተርጎሙ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 25(3) ስር በብዙ ቁጥር አገላለጽ በሚገኙ እያለ ማንኛውም ችሎት ብሎ በነጣለ ማስቀመጡ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 27(2) ስር የአማርኛው ቅጅ የስር ፍርድ ቤት መዝገብን ሰበር ችሎቱ ማስቀረብ እንደሚችል ሲገልጽ መዝገቡን የሚያስቀርበው በራሱ በኩል መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ ደንግጎ እያለ በእንግሊዝኛው ቅጂ ግን ችሎቱ መዝቡን የሚያስቀርበው በተከራካሪ ወገኖች በኩልም ሊሆን እንሚችል መደንገጉ፣

o በአንዳንድ አንቀጾች የፍርድ ቤቶቹን ስያሜ በእንግሊዝኛ ሲጠቅስ የመጀመሪያ ፊደላትን ካፒታላይዝ ለምሳሌ በትልቅ ፊደላት/capital letters/ Federal High Court ይልና ትንሽ ቆይቶ ደግሞ በትንሽ ፊደላት(Small) federal high court ብሎ ማስቀመጡ(ምንም እንኳን መሰረታዊ ባይሆንም ወጥነት የሌለው የስም አገላለጽ በመሆኑ ተገቢነት የለውም..)፣

o በአዋጁ አንቀጽ 34(5) ስር የአማርኛው ቅጅ ቀናት ማለት ሲገባው ቀን ብሎ ጠቅሶ ካለፈ በኋላ የእንግሊዝኛው ቅጅ days ብሎ መተርጎሙ፣

ALE (አለ) law societies :

o በአንዳንድ ድንጋጌዎች ስር የአማርኛ ቅጂው ላይ ቁጥር ሲኖር ቁጥሩ በኢትዮጵያ(በግዕዝ) አኃዝ እየተቀመጠ ከሄደ በኋላ በአንዳንድ ድንጋጌዎች ደግሞ በፊደል ብቻ የተቀመጠ ሁኖ መገኘት(ለምሳሌ አንቀጽ 52)፣

o በአዋጁ አንቀጽ 53(3) የአማርኛው እና የእንግሊዝኛው ቅጅ የማይጣጣሙ መመስል፣ የአማርኛው ቅጅ እያንዳንዱ የአማካሪ ምክር ቤቱ አባል በግል ደረጃ ኃላፊነቱን ሲወጣ ስለሚኖረው ግዴታ የሚያውጅ የሚመስል ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጅ ግን አማካሪ ምክር ቤቱ እንደተቋም ያለበትን ግዴታ የሚያሳስብ ይመስላል፣

o በአንቀጽ 35(2) ስር የቅጣቱን መጠን ከሺህ እስከ፪ሺህ ብሎ አስቀምጦ እያለ እና ይህ አገላለጽ መነሻውንና ጣሪያውን የሚያሳይ ሁኖ እያለ በድጋሚ በአርፍተ ነገር ከአንድ ሺህ ብር ያላነሰ ከሶስት ሺህ ብር ያልበለጠ ማለቱ እንዲሁም ከ፪ሺህ እስከ ፯ሺህ የሚለውንም ከሶስት ሺህ ብር ያላነሰ ከሰባት ሺህ ያልበለጠ ብሎ አላስፈላጊ በሆነ አገላለጽ መጠቀሙ፣ በዚሁ ድንጋጌ ስር በቁጥር የተቀመጠውን መነሻ እና ጣሪያውን በአረፍተ ነገር ሲያስቀምጥም ቅንፍ ከፍቶ የዘጋበት ቃል ትክክለኛ ያለመሆኑ(ቅንፉ ሲዘጋ ያልበለጠ በሚለው ቃል መጨረሻ ላይ ያለመቀመጡ፣

o በአዋጁ አንቀጽ 26(4) ስር ባለሰባት ዳኞች ሰበር ችሎት የራሱን ውሳኔ ሊያሻሽል እንደሚችል የሚገልጽ ድንጋጌ እያስቀመጠ በድንጋጌው የመጨረሻ አረፍተ ነገር ፊደል... ያ... ቀሪ ተደርጋ ሊሻሻል ይችላል ተብሎ መቀመጡ፣(ሊያሻሽል..... መባል የነበረበት ይመስለኛል).

2.3 አዋጁ ስለሰበር የሕግ ትርጉም አስገዳጅነት የሚገልጽበት አግባብ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ብቻ እንደሆነ የሚያስመስል መልዕክት የሚያስተላልፍ መሆኑ

 በአዋጁ አንቀጽ 10(2) ስር የሰበር ችሎቱ የሚሰጠው የሕግ ትርጉም አስገዳጅነቱ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 2(5) ደግሞ የመጨረሻ ውሳኔ የሚባለው በፍርድ ቤት የተሰጠ ብቻ ያለመሆኑን የሚያስገነዝብ ድንጋጌ ይዟል። ስለሆነም ሁለቱ ድንጋጌዎች እንዲሁም አንቀጽ 2(4(ሰ)) ድንጋጌ መጣጣም ይገባቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ የህግ ትርጉም አስገዳጅ እንዲሆን ከፈለገበት ዓላማና ችሎቱ ሲከተለው ከነበረው፣ አሁንም እየተከተለ ካለው አሰራር አንጻር የሕግ ትርጉሙ ለፍርድ ቤት፣ በሕግ የመዳኘት ስልጣን በተሰጣቸው አካላት፣ ተቋማትና አማራጭ የክርክር መፍቻ ሰጪ አካላት ጭምር አስገዳጅነት እንዲኖረው ግልጽ መደረግ ነበረበት። ለግልፅነት ብዬ ያነሳሁት እንጂ እነዚህ ተቋማት የሰበር ችሎቱን የህግ ትርጉም ተቀብለው ተግባራዊ ማድረግ አንችልም ማለት ይችላሉ ለማለት አለመሆኑ ይታወቅልኝ።

2.4 መከተት የነበረባቸውን ጉዳዮች የተወ መሆኑ

 የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ስህተት የሚባለው ምን እንደሆነ ትርጉም ማስቀመጥ ወይም አመላካች ነጥቦችን ጠቅሶ ያለማለፉ፣ በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ተጠቃሽ ነው።

 በሰበር ችሎቱ የተሰጠ የህግ ትርጉም ለአንድ ጉዳይ አስገዳጅ ነው የሚባለው በመሰረታዊ ሕግና በፍሬ ነገሮች መካከል መመሳሰል ሲኖረው መሆን ያለመሆኑን ጠቅሶ ያለማለፉ፣

 የሰበር ችሎቱ ዳኞች በህግ ትርጉሙ የሚገደዱ መሆን ያለመሆናቸው፣(ምንም እንኳን ዳኞቹ ከሌሎች የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች የተለዩ ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ቢታወቅም ለክርክር በር ይከፈት የነበረ ጉዳይ መሆኑ ይታወቅ ስለነበር መፍትሔ ተበጅቶ ቢታለፍ መልካም ነበር)፣

 የሰበር ችሎቱ ውሳኔ ለመቀየር የሚቻልባቸው ምክንያቶች አመላካች በሆነ መንገድ(ለምሳሌ ተቃራኒ ውሳኔ መኖር፣ ሶሺዮ ኢኮኖሚክ ፋክተርስ...) ተጠቅሰው ያለማለፍ፣

 ውሳኔውን ለመቀየር ሲያስፈልግ አቋሙ መያዝ ያለበት ከአምስቱ ዳኞች በስንቱ ዳኞች እንደሆነ ተለይቶ መቀመጥ ነበረበት፣ እንዲሁም ተጨማሪ ሁለት ዳኞች ወደ ችሎቱ የሚገቡበት ከሌሎች የሰበር ችሎቶች ውስጥ ነው ወይስ ከይግባኝ ችሎቶች ጭምር የሚለውም(ምንም እንኳን ሁሉም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚሾመው በተመሳሳይ መመዘኛ ስለሆነና ዳኞችን መመደብ የፍርድ ቤቱ የአስተዳደር ኃላፊነት ቢሆንም ከችሎቱ ልዩ ስልጣን አንጻር ለግልጽኝነት ሲባል ቢቀመጥ መልካም መስሎ ይታያል)፣

 በሰበር ችሎቱ የሚደረገውን የጽሑፍ ክርክር ሬ/ጽ/ቤት ማከናወን የሚችል መሆኑ(በአሰራር ያለ ቢሆንም እንዲሁም ወደፊት በጋይድላይን ሊወጣ የሚችል ቢሆንም)

 አዋጅ ቁጥር 322/95 አዲስ ክልል ሲፈጠር ስለሚኖረው ህጋዊ ውጤት

o ለምሳሌ በዚህ አዋጅ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተቋቋመባቸው ክልሎች አንዱ የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት አንዱ ሲሆን ከዚህ ክልል ውስጥ የሲዳማ ክልል ተፈጥራል። ስለሆነም የሲዳማ ክልል የደቡብ ክልል አካል ስለነበር በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቋቁሞበታል ሊባል ይችላልን የሚለው ጥያቄ በቀላሉ የሚመለስ ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም።

 እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተቋቋመባቸው ክልሎች ውስጥ የፌዴራሉን መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በውክልና የሚያዩት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት ውሳኔ ይግባኙ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆን ያለመሆኑም በዚህ አዲስ አዋጅ ምላሽ ማግኘት ይገባው ነበር። ይህ እንዳይሆን የሚከለክል የሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ውሳኔ ስላለ።

2.5 ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዮች ያሉበት መሆኑ

አዲሱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ለአዲስ አበባና ለድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች በወንጀልም ሆነ በፍትሃ ብሔር ጉዳዮች ስልጣን ሰጥቷል። የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት የተቋቋሙ መሆን ያለመሆኑ አከራካሪ ጥያቄ ከመሆኑም በላይ እነዚህ ፍርድ ቤቶች ከፌዴራል ስርዓት ጽንሰ ሀሳብ አንጻርም ፍርድ ቤቶቹ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር የተያያዙ ጉደዳዮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ከሚኖራቸው በስተቀር የፌዴራል ጉዳዮችን እንዲዳኙ የሚደረግበት የሕግ አግባብ ያለ አይመስለኝም። እንዲሁም ህገ መንግስቱ የሰበር ሰበር እንደሚኖር የሚያሳይ ድንጋጌ ይዞ እያለና ይህ ደግሞ ሕገ መንግስቱ ሲረቀቅ በነበረው ውይይትም በግልጽ ተነስቶ አረቃቂው አቋም ይዘበት ያለፈው ሁኖ እያለ በአዲሱ አዋጅ የክልል ጉዳዮች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታዩበት መንገድ እጅግ ጠባብ እንዲሆን መደረጉ ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ የሚያስነሳ መስሎ ይታያኛል። የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በርካታ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ጉዳዮች እንዲመለከቱ እንዲሁም የሰበር ሰበር ስርዓት እድል እጅግ ጠባብ እንዲሆን የተደረገበት አቢይ ምክንያት ግልጽ የሆነ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ስላለ ሳይሆን በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያጋጠመው የመዝገብ ክምችት ይመስለኛል። የመዝገብ ክምችት ማጋጠም ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡትን ጉዳዮች ለመከልከል/ ለመገደብ ወይም የፍርድ ቤቱን ስልጣን ለሌላ አሳልፎ ለመስጠት ህጋዊ ምክንያት ሊሆን አይችልም።

ALE (አለ) law societies :

3. ማጠቃለያ

ጠንካራ ፍርድ ቤት ለአንድ አገር ብልፅግና ወሳኝ ሚና አለው። ጠንካራ ፍርድ ቤት የሚኖረው ደግሞ የፍርድ ቤቱን ነፃነትና ገለልተኝነት የሚያረጋግጥ ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ሲኖርና የወጣው ህግም በትክክል ሲተገበር መሆኑ ይታመናል። በእኛ አገር ነጻና ገለልተኛ ፍርድ ቤቶች እንደሚኖሩ በሕገ መንግስቱ ጭምር የተደነገገ ቢሆንም በህገ መንግስቱ አግባብ የተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ለበርካታ ጊዜያት የተለያዩ አዋጆች ሲወጡላቸው የነበሩ ከመሆኑ ውጪ ነጻና ገለልተኛ ነበሩ ለማለት እያስደፍርም። ለዚህ ትልቁ ማሳያ ደግሞ ፍርድ ቤቶቹ የራሳቸውን በጀት ማስመደብና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የማስተዳደር ስልጣን ያልነበራቸው መሆኑ ነው። አሁን የወጣው ሕግ ግን እነዚህን ችግሮች አስወግዷል። ይህም ትልቅ እምርታ ነው። በዚህም ለፍርድ ቤቶቻችን ነጻነታቸውና ገለልተኝነታቸው ማሳኪያ የሚሆን ትልቁ ሐዲድ ተገንብቶላቸዋል ማለት ይቻላል። በሐዲዱ መጓዝ እና ወደ መዳረሻው መድረስ ደግሞ የፍርድ ቤቶቹ አመራሮች፣ ዳኞችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ኃላፊነት ይሆናል። ከላይ የተጠቀሱት የአዲሱ አዋጅ ችግሮች መሰረታዊ ሊባሉ የማይችሉ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ህግ በአንድ ተቋም መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ታስቦ ሲወጣ ትልልቅ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ፣ በአሰራር ሂደት ያጋጠሙትን ችግሮች መቅረፍ እና ረዥም አመታት ሊያሰራ የሚችል/ ዘመን ተሻጋሪ ሁኖ መቀረፅ ያለበት መሆኑ የሚታመን ከመሆኑም በላይ ሕጉን የማርቀቅ ስራም/Drafting Task/ የዘርፉን ጥበብ ባሟላ መልኩ ከአርትኦት፣ ከቋንቋ ትርጉም ግጭትና ከይዘት መጣጣም እና ከሌሎች ተያያዥ ችግሮች የጸዳ እንዲሆን ተገቢው ጥንቃቄ ይጠይቃል።

Via alamaw wele